# እናልቅስ ወይስ እንሳቅ?

## ከግባችን የሚያደናቅፉንን እንንቃባቸው!

ከመዝገበ ባየህ

የወያኔው መሪ በሰሜን አፍሪክና አርብ ሀገሮች የተከሰተው ሕዝባዊ አመጽ እኔም ጋ ይመጣል ብሎ በመስጋት የሕዝብን ዕይታ ወደ ሌላ ለመሳብ ሲል አዲስ የአባይ ድልድይ እንገንባ ብሎ አላስፈላጊ ክርክርና አደናጋሪ ዘመቻውን አጧጡፏል። ነቅተንበታል ግን። የኢትዮጵያ ሕዝብ ትኩረት በሕዝባዊ ኣመጽ ላይ መሆን ሲገባው፤ ይህን አመጽ በማደራጀትና ሊያደራጁ በሚችሉ ሀይሎች ላይ ሊሆን ሲገባው፣ ከኦነግና ኦብነግ ጋር መተባበር አለብን የሚል ርባና ቢስ ጭቅጭቅና ክርክር ያነሱት ክፍሎች እነሆ በውጭ ሀገር ነዋሪ የሆነውን ዜጋ ዕይታ አጓጉል አድርገውታል። ይህ የተባለው ትብብር ለሀገርም ለሕዝብም የሚበጅ አይደለም ሲባሉም ድርጅትን ለማፍረስ መፍጨርጭር ልምዳቸው የሆነና በአፍ ይጠፉ በለፈለፉ አንዳንዶች ደግሞ ምላሽ ሰጥተው አቅዋማችውን በመከላከል ፈንታ የፈረደበትን ኢሕአፓንና መሪዎቹን መዝለፉን ተያይዘውታል። ለወያኔ ጥቅም እየሰጡ እያገለገሉ ማለት ነው። ይህን ርዕስ ወደታች ሰፋ አድርጌ እመለስበታለሁ።

ሌላው እናልቅስ ወይስ እንሳቅ የሚያሰኘን ጉዳይ ደግሞ በቅርቡ ራሱን ብሔራዊ የወጣት ማህበር ብሎ በሚጠራውና ማስረሻ ጥላሁን የሚባል ግለሰብ እመራዋለሁ የሚለው “ቡድን” ያወጣውን መግለጫ ይመለከታል። ይህ “ቡድን” እውን ህልውና ይኑረው፤ አለዚያም እንደሚታማው የአንድ ፖቲካ ድርጅት ጭምብል ይሁን ወይም ሌላ እስካሁን አነጋጋሪ ነው። ለማንኛውም መሪ ነኝ የሚለው ግለሰብ ከዚህ ቀደም "በቃ" በሚል መፈክር ስር የሕዝባዊ አምጹን ቀን ቀጠሮና ቦታ ወስኖ ተቃዋሚውን ሁሉ ያሳፈረ መሆን የሚታውቅ ነው። በዚህ አባሪ

ባደረግነው የአሁኑ መልዕክቱ ደግሞ ትግሉን በሶስት ደረጃ ፈርጆ የመጀመሪያው ማለቂንና ቀጣዩ የተጨባጭ አመጹ ጊዜ ደግሞ ከመስከረም በኋላ ጀማሪ መሆኑን (በመስቀል በዓል ወዘተም ሊፈነዳ መዘጋጀቱን)፣ በሀገር ቤት አመርቂ ድርጅታዊ ስራ እየተሰራ መሆኑን፣ ለዚህም ዜጎች ገንዘብ መለገስ እንዳለባቸው ጽፏል። ቀደም ሲል ደም ገብሮና መከራን ተቀብሎ የሚገኝን አርበኝነት በ 500 ዶላር እንስጣችሁ ያሉትን እናስታውሳለን። ይህ በወጣት ድርጅት ስም የወጣውም ጥሪ ተመሳሳይ ከመሆኑ ሌላ የሀገራችንን ሁኔታ የምናውቀው ሁሉ በድረ-ገጽ የሚጠራና የሚቀጠር አመጽ መሳቂያ ያደርገናል እንጂ ውጤት እንደማይኖረው እናውቃለን። ነገሩ ሁሉ ያስቃል። ግን የሀገር ጉዳይ ነውና ያስለቅሳልም። በሕዝብ ትግል መቀለዱ ቢያበቃ ምን አለ? የዚህ ወጣት አለቆችም ተው፣ በቃህ እረፍ ቢሉት ምን አለበት?

ወደ ዋናው ነጥባችን ስንመለስ ወያኔ የአባይ ግድብን ግንባታ ጉዳይ በማንሳትና በዚህ ዙሪያም ካድሬዎቹን በማስጮህ ሕዝብ ወደ አመጽ እንዳያተኩር ለማድረግ ችሎ ነበር። ማደናገር ይሿል ይህ ነው። ከኦነግ ጋር ትብብር ያስፈልጋል ብለው ጥያቄውን ያነሱት ክፍሎች ዓላማቸው የዜጎችን ዕይታ ከዋናው የአምጽ ጉዳይ ለማራቅ ላይሆን ቢችልም ተጨባጭ ውጤቱ ግን ይህ መሆኑ ግልጽ ነው። ለወራት ንትርክና እሰጥ አገባው በዚሁ ጥያቄ ዙሪያ ሆኗል። ወያኔ ተረስቷል ቢባል ስህተት አይሆንም። በድርጅቶች መሀልም ሊኖር የሚገባው መቀራረብ ጠፍቶ በንትርክ ተተክቷል። ይህም ለአፍራሽ ሀይሎችና ለወያኔ ሰርጎ ገቦች አመቺ ሁኔታ ፈጥሮላቸዋል። ሀላፊነት የጎደላቸውና ነገር ዓለሙን ማደፍረስ ስራቸው የሆነ ግለሰቦችም ወደ መድረክ ብቅ ብለው መበጥበጥ ችለዋል። ስለ ትብብር መነሳቱ ከትግል ጋር የተያያዘ ነው። ግን ባለንበት ሁኔታ የትብብር ትኩረት በአንድነት ሀይሎች መሃልና ወደ

አመጽ ማደራጀትም ያተኮረ መሆን ነበረበት። ይህን ካልን በኋላ ደግሞ ክርክሩም ቢሆን ከነኦነግ ጋር መተባበር ይጠቅማል? ኦነግ እንደሚባለው አቅዋም ቀይሯል? የሚለውን መመልከት ይገባዋል እንጂ በጥባጮቹ እንደሚፈልጉት ድርጅቶችን መደብደቢያ መሆን አይገባውም። ከ ኦነግ ጋር መተባበር ያስፈልጋል የሚለውን አቅዋም ለሕዝብ መሸጡ ካቃተ ኢሕአፓን መስደቡና ይውደም ማለቱ  ምንም ጥቅም የለውም። ይህን የተሳሳተና ለገንጣዮች የሚስማማ ኣቅዋም በስፋት የተቹት ዜጎች የሚታውቁና ራሳቸውን የቻሉ ናቸውናም የድርጅት አባልነትን በራሳቸው ላይ አላግባብ መጫንም አሳዛኝ ይሆናል። አንድ ድርጅትንም ሁሉን ከሀሊ፤ፈጣሪ፤ ዘዋሪ፤ ጸሐፊ ወዘተ አድርጎ ማቅረቡም ስህተት ከመሆኑ ሌላ የራስንም የዝቅተኛነት ስሜት አጋላጭ ነው። ቀድሞውኑ አፍ ሲያመልጥ መቆጣጠር፤ ይህ ካልተቻለ ደግሞ አጠፋሁ ብሎ በድፍረት ይቅርታ መጠየቅ እንጂ የራስን ቀውስ ወደሌሎች ለመጫን፣ ለማዛወር መጣሩ ከንቱነት ነው።

ይህን ለወያኔ እየጠቀመ ያለን ንትርክ ለማስቆም ሀገር ወዳድ ዜጎች መንቀሳቀስ አለባቸው። እንደምንሰማው ከሆን ልዩ ልዩ የዕርቅና የህብረት ጥረቶች ኣሉ። ሁሉም የሚያበረታቱ ናቸው። ጸረ ወያኔ ሀገራዊ ሀይሎችን ሊያስተባብር የሚችል ጥረት ሁሉ መደገፍ አለበት። ካለፈው ተመክሮም በመማር አፍራሾችን አግልሎ ታጋዮችን ማቀራረብና ማስተባበር ያስፈልጋል። በየድረገጹ ያሉ ተሳዳቢዎችና ከፋፋይ ግለሰቦች፡ ወንጀለኞች፡ መለስን ጠላን ቢሉም የዘረኘነት አቀንቃኞችን ሁሉ ማግለል ተገቢ ነው። በቀይ ሽብር ወንጀል የሚፈለጉ ወይም የተፈረደባቸው አረመኔዎች ዛሬ ተደብቀው በኢሕአፓ ላይ ዘመቻቸውን ሲያጧጡፉ በዝምታ ማየትም አይገባም። ኦነግ ኦነግ ነው። አቶ ዳውድ ኢብሳም በቅርቡ ለባን ኪ ሙን በጻፈው ድብዳቤ ግልጽ

አድርጎታል። የተለወጠ የለም-- እርዱኝ ልገንጠል ነው የሚለው። ኦብነግማ ኢትዮጵያዊነት ስድብ ነው ካለ ውሎ አድሯል። ከነዚህ መወያየት ስህተት ነው ያለ የለም። ለነዚህ የትሮጃን ፈረስ መሆን ወይም በራሳችን የቁርጥ አነጋገር ደግሞ መጋዣ መሆን ግን ስህተት ነው ተብሏል። ሀቅ ነው። እንወያይ እንቀራረብ ማለት ሳይሆን ስህተቱ ባልተቀየሩብት ተለወጡ ብሎ መዋሸት ነው። ለውጥ አድርገዋል ብሎ መቀባጠሩ ነው ውሸቱ። ውሸቱ እነሱ ያልሆኑትን ናቸው ብሎ ያልሆነ ገጽታ በመስጠት ሕዝብን ማዘናጋት ነው።  ስህተቱ በውሸት ቀለም ቀባብቶ፣ በትብብር መድረኮችን አዘጋጅቶ፣ የነገን ሀገር በታታኞች ማጎልበት ነው። ወንጀሉ - አንድ ታዛቢ እንደፃፉት — በአንድነት ስም አንድነትን  ለመግደል መዝመት ነው።  የራስን ቅሌት በሌላ ድርጅት ላይ ለመጫን መቅበዝበዝ ነው ስህተቱ።  ወንጀሉ የሀገርን ህልውና፣ የዚህም ቋሚ መገለጫ የሆኑ ታሪካዊ ቅርሶችን ለምሳሌ ሰንደቅ ዓላማን ማንሳትና ከጥፋት መከላከል ሃጢአት ተደርጎ፣ የኢትዮጵያዊነትን ቅስም ለመስበር የሚደረገው ዘመቻ ነው።

ሌላው መሳቂያ ደግሞ ዶክተር ዜሮ ነው — ከሰሞኑ እራሱን የመወያያ ርዕስ ለማድረግ በመሞከር ላይ ያለው።  ሀገርን ያህል አንስቶ በአደባባይ እየደሰኮረ፣ ያውም ነበርኩበት ከሚለው ህብረ-ብሄር ወገን ተስፈንጥሮ ወደ ጎሰኞች ወገን (ካምፕ) ገብቶ፣ ሀገር ቅርጫ ካልገባች እያለ፣ "አታንሱኝ! የሹም ዶሮ ነኝ!" ሊል ባልተገባው ነበር።  ታዋቂው ገጣሚ ከዚህ በታች እንዳለው፣ "ምን ያለበት ዝላይ አይችልም" እንዲሉ ሆኖ ነው እንጂ።  በትግል ዓለም ጥሩ ምግባር ካለ እንደ ጽጌረዳ እየፈካ፣ መጥፎም  ከሆነ እንደ ጥንብ እየገማ ስምን ማስነሳቱ የግድ ነው።   ለማንኛውም ቀደም ሲል ባነሳሁት ድንቅ ገጣሚ ስንኞች ልደምድም፡

ቦርቡሮ! ቦርቡሮ! ሲያቆስለኝ ከርሞ፣
ተንሰራፍቶ ኑሮ፣ በእኔ ላይ ደምሞ፣
ያ!... የተገላገልኩት፣ ያ!... የሻርኩት ኮሶ!
ከጉድጓድ ተቀብሮ፣ የኖረው በስብሶ፣
ዳግም ተመልሶ፣ ከዘር ተቀላቅሎ፣
ችፌ ሆኖ በቅሎ!
ጡንቻ አልፈስፍሶ፣ አቁስሎ አቆሳስሎ!
ሊያሽመደምደኝ፣ ሲለፋ ቀን ሌሊት፣
ደብተራው በሰጠኝ፣ የሀገር መዲሃኒት፣
ወገን ተመርኩዤ፣ በሁለት እግሬ ቆሜ፣
በምድር እንቡአይ ቅጠል፣ ደምድሜ! ደምድሜ!
ግልጥልጥ አድርጌ፣ አስጥቼው አደባባይ!!
እንዳይሸፋፈን፣ እንዲመታው ፀሐይ፣
ወጪ ወራጅ ሁላ፣ ሲያየው ተጠይፎ!
ግማቱ ቀለለኝ፣ ተገላገልኩ ረግፎ፣
አንተ! ክፉ! ባክቴሪያ! በሞቀበት በቃይ!
የሰው ስጋ በላ፣ ደካማውን ፈንጋይ!
አቅሜን ሳትበላው፣ ጉልበቴን ሰርስረህ!!
ችፌ! ሙት ደሳለኝ፣ በምክሰምህ ቀድመህ!
ያ!! ችፌው ደሳለኝ!! ሲከስም አየሁት!!
ግማቱ ቀለለኝ፣ በድጋሚ ሻርኩት!!!
ከእንግዲህስ ወዲያ፣ እርም የሰውን ስጋ!!
ጥንብ አንሳ! ካልሆነ፣ የለም የሚያስጠጋ፣
ከብቶችም ላይ አትችል፣ አበቃልህ ችፌ!
እኖራለሁ አትል፣ በሰው ዘር ታቅፌ፣
ያኔ! ስለሻርኩህ፣ ግምኛው ቀለለኝ!
አኪርህ ተቃጥሏል፣ ከእንግዲህ ደሳለኝ!!!!

ስለኢትዮጵያ አንድነት የሚያስብ ቸር ይሰንብት!

ክብር ለአንድነት ሰማዕታት!

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

mezigebeb@hotmail.co.uk

**ጠላትን በቀጠሮ?!**

**ጉደኛው አባሪ**

# Press Release — Ethiopian Youth National Movement

73
Like

Human Rights, Freedom and Democracy should not be revolutionary concepts in this day and age, but similar to the struggles of other youth in the Middle East and parts of Africa, we are struggling to have them become more than just a dream but a reality for All Ethiopians. The winds of change have reached our borders and planted seeds of hope, that we as Ethiopian Youth must seize, to demand a better opportunity and way of life, for ourselves and for the future of Ethiopia. The era of tyranny and despotism is coming to an end in nations across the globe and so to must it end in Ethiopia! We the Ethiopian Youth National Movement (EYNM) are working to help facilitate this change and have established two critical goals to achieve our objectives: 1) Regime change through peaceful uprising and 2) Establishment of a transitional government that can pave the way to free and democratic elections.

Our first goal of overthrowing the dictatorial regime of Meles Zenawi will be accomplished in three phases (objectives). The first phase of our mission, which begun on the 28th May 2011, was to plant fear and intimidation in the regime and agitate the Ethiopian youth. We are proud to declare that this objective has been fulfilled. The regime's high level of intimidation towards any movement by Ethiopians has been evident in their preparation for violent response against peaceful demonstrators. As another clear manifestation of the regime's fear of the people, it is currently carrying out random mass arrests of young Ethiopians all over the country. Nevertheless such brutalities on the regime's part will prove to be futile in stopping our Movement from bringing an inevitable end to Meles' tyrannical rule.

We are currently planning the details of the second phase of our struggle, which will be a period of mass uprisings and demonstrations. This phase will run from September 2011 to December 2011. Of particular use to our mass uprising phase will be taking advantage of some Ethiopian national public events, such as: the famous Meskel Celebration (September 27, 2011) and the Great Ethiopian Run (November 19, 2011). This year, the aim of these national events will be changed so as to reflect the people's frustration at the regime and to fuel further mass uprisings.

Although we plan for the demonstrations to begin from the start of September 2011, we hope to use the Meskel celebration to bring this revolution to the attention of all segments of our people and the world at large. The Meskel celebration includes the burning of a large bonfire, or Demera. While many believe that the Demera, marks the ultimate act in the cancellation of sins, mystics of old tradition hold that the direction of the smoke and the final collapse of the heap indicate the course of future events. This year, Ethiopians will burn TPLF's dictatorship in the fire along with all the sins that it has committed against our people. Ethiopians will be singing revolutionary songs and chanting revolutionary slogans against the regime. Ethiopian youth will highjack this celebration to clearly display their anger at the regime and demand their country back. Another great opportunity similar to the above is the Great Ethiopian Run on November 19th, 2011. This is Africa's greatest 10Km run. We will change the theme of the run this year to: "Run for freedom and democracy in Ethiopia."

Our revolution requires large number of people, strict discipline and code of ethics, strategic and systematic planning at all levels, and massive recruiting and substantial worldwide attention. The EYNM is an independent and global Ethiopian youth movement, multiplying exponentially in Ethiopia and throughout the world, and conducting various small and large campaigns to weaken the regime. We ask all Ethiopians to join us in our future mass demonstrations, civil resistances and various campaigns so that we can change the fate of our people. No change will come from sitting idle and waiting for it to come. All Ethiopians, civic and political organizations should support our effort to overthrow what will be the last dictator in Ethiopia, Meles Zenawi, once and for all.

Ethiopian Youth National Movement

**Please consider the following donation options:**

1. **Active Sponsor** - (30/month or above)
2. **Active Supporter** - ($20/month or above)

## 3.Donor

- **Elite class** - $5000 and More
- **Platinum** - $1000-$5000
- **Gold** - $500-$1000
- **Silver** - $100-$500
- **Bronze** - $25-$100